DC DEPARTMENT OF HUMAN SERVICES

# INFORMATION AND FACTS ABOUT
# የቤት እጦት እያጋጠማቸው ያሉ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች የማረጋገጫ ጊዜ ማራዘሚያ

## የቤት እጦት እያጋጠማቸው ያሉ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች አሁን ያለው የማረጋገጫ ጊዜ ምን ያህል ነው?

በአሁኑ ጊዜ፣ በዲስትሪክቱ ቤት እጦት እያጋጠማቸው ያሉ ቤተሰቦች የ6 ወር የማረጋገጫ ጊዜ ተሰጥቷቸዋል።

## ቤት እጦት እያጋጠማቸው ላሉ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች አዲሱ የማረጋገጫ ጊዜ ምን ያህል ይሆናል?

ከዲሴምበር 2023 ጀምሮ፣ ዲስትሪክቱ የቤት እጦት እያጋጠማቸው ላሉ ሁሉም ቤተሰቦች የ12 ወር የማረጋገጫ ጊዜ ለመስጠት አቅዷል።

## የቤት እጦት እያጋጠማቸው ያሉ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች ስለዚህ ለውጥ ማስታወቂያ የሚደርሳቸው እንዴት ነው?

በጁላይ 2023 ማብቂያ ላይ፣ DCAS/DHS SNAP ለሚቀበሉ ሁሉም የቤት እጦት ላጋጠማቸው ቤተሰቦች የሚከተሉት ነገሮች በተመለከተ ለማሳወቅ ማስታወቂያ ልኳል፦

- የማረጋገጫ ጊዜያቸው ለ12 ወራት ተራዝሟል።
- አዲሱ የጥቅማጥቅም ማብቂያ ቀናቸው እስከሚደርስ ድረስ (በማስታወቂያው ላይ የሚታይ ይሆናል) እንደገና ማረጋገጥ አያስፈልጋቸውም።
- ሚድ-ሰርቲፊኬሽን ቅጽ ለመሙላት የሚያስፈልጉ መስፈርቶች።

## ይህ የቤት እጦት እያጋጠማቸው ላለ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች ምን ማለት ነው?

የቤት እጦት እያጋጠማቸው ላሉ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች እስከ አዲሱ የጥቅማጥቅም ማብቂያ ቀን ድረስ እንደገና ማረጋገጥ አያስፈልጋቸውም። የድጋሚ ማረጋገጫ ማመልከቻ ለማስገባት ጊዜው ሲደርስ ለማስታወስ ማስታወቂያ እንልክልዎታለን።

## የቤት እጦት እያጋጠማቸው ላሉ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች የሚድ-ሰርቲፊኬሽን ቅጽ ቀነ ገደብ ማስታወቂያ እንዴት ይደርሳቸዋል?

የቤት እጦት እያጋጠማቸው ያሉ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች የተያያዘውን ሚድ-ሰርቲፊኬሽን ቅጽ ለመሙላት የተለየ፣ መስፈርታቸውን የሚያሳውቅ ከስርዐት የመነጨ ማስታወቂያ ይደርሳቸዋል።

ሚድ-ሰርቲፊኬሽን ቅጹን እና የለውጦችን ማረጋገጫ እስከ ቀነ ገደቡ ድረስ ለሚመጣው ኢጋማሽ ማረጋገጫቸው ካልመለሱ፣ የSNAP ጥቅማጥቅሞች ሊቆሙ ይችላሉ።

## የቤት እጦት እያጋጠማቸው ያሉ SNAP የሚቀበሉ ቤተሰቦች ጥቅማጥቅሞቻቸውን እንደገና የሚያረጋግጡበት ማስታወቂያ ሲደርሳቸው ምን ማድረግ አለባቸው?

የድጋሚ ማረጋገጫ ማስታወቂያ ከደረሳቸው በኋላ፣ ቅጹን በመስመር ላይ ይሙሉ - https://districtdirect.dc.gov/ua/ ወይም የSNAP ጥቅማጥቅሞችን ላለማጣት ዳግም ማረጋገጫን ለማሙላት የአካባቢያቸውን የአገልግሎት ማዕከል ይጎብኙ።

- በኢንተርኔት። https://districtdirect.dc.gov/ua/ ይጎብኙ ወይም የDistrict Direct መተግበሪያን ከ Google Play ወይም Apple app stores ያውርዱ።

- በአካል። የአገልግሎት ማዕከላት ከ7:30 a.m.–4:45 p.m.፣ ከሰኞ እስከ አርብ በሚከተሉት ቦታዎች ክፍት ናቸው፦

**ANACOSTIA የአገልግሎት ማእከል**

2100 Marthin Luther King Jr. Ave. SE, DC 20020

Congress Heights የአገልግሎት ማእከል

4049 South Capitol St. SW, DC 20032

**FORT DAVIS የአገልግሎት ማእከል**

3851 Alabama Ave. SE, DC 20020

H Street አገልግሎት ማእከል

645 H St. NE, DC 20002

**TAYLOR STREET አገልግሎት ማእከል**

1207 Taylor St. NW, DC 20011

## ደንበኞች ተጨማሪ ጥያቄዎች ካላቸው ወይም ተጨማሪ እርዳታ ከፈለጉ ማንን ማነጋገር ይችላሉ?

ለመረጃ እና ለጥያቄዎች፣ ደንበኞች ወደ ህዝብ ጥቅማጥቅሞች የጥሪ ማዕከል በ202-727-5355 ወይም TTY 711 መደወል ወይም https://dhs.dc.gov/service/supplemental-nutrition-assistance-program-snapን መጎብኘት ይችላሉ።